


# ያቺ ድሪ

ሥርጉተ ሥላሴ

ያች ድሪ
ያልሆነች ፈሪ
ተስፋነን ዘሪ።

ያች ዕንቁ
የህግ ዕንቁ
ሀሰትን አውልቁ።

ያች ጀግና
ያላት ዝና
የተግባር መና።

ያች ፈርጥ
የአንስት ጌጥ
ሀቅ እምትንጥ።

ያች ተፈሪ
ፍቅርንን አድሪ
ፅናትን አብሪ።

ያች ፍቅር
የትግሉ ገበረ
የመስዋትነት አድባር።

ያቺ ደፋር
የቆራጥነት መንበር
ፍሬ ዘር።

... 2

**ያቺ ነፍስ**
**ቅዱስ መንፈስ**
**እንባን አበስ።**

**ያች ብርቴ**
**የዕውነት ዕትብቴ**
**የትግሰት ሚተቴ።**

**ያች ህብስቴ**
**የአርነት ምልክቴ**
**የሴቶች ክብርቴ።**

**አንበሳዋ እህቴ**
**የእኩልነት ሚተቴ**
**የፍፁም ታማኝነት ፏፏቴ**

*ጥር 12 ቀን ሂርሽን ሆቴል*
*ሥጦታ ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ  የአንድነት ሊቀመንበር*